# መረጃ

የአሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
2009/35B
Tel. (011) 517-4007 Fax. (011) 124-2454

ለተ□ ማሪ መረ□ : 011-517-4308.
የኢንተርኔት አድራሻ: http://ethiopia.usembassy.gov


# ጥያቄ እና መልስ

## የ2011 የዳይቨርሲቲ ቪዛ መርኃ ግብር ለኢትዮጵያ

**የአሜሪካ ዳይቨርሲቲ ቪዛ ፕሮግራም ምንድን ነው?**

በአሜሪካ ኮንግረስ በተሰጠው ስልጣን መሠረት፣ የዩናይትድ ስቴትስ ዳይቨርሲቲ ኢሚግራንት ቪዛ ፕሮግራም ከመላው ዓለም በአሜሪካ የሚኖሩ ዜጎቻቸው ቁጥር አነስተኛ ለሆኑ አገራት በየዓመቱ በሚወጣ ዕጣ አማካይነት ዕድሉ ለሚደርሳቸውና በፕሮግራሙ የሚጠበቀውን ለሚያሟሉ አመልካቾች 50000 የዲቪ ዕጣዎችን በማውጣት በአሜሪካ የመኖርና የመስራት ዕድል የሚያስገኝ መርኃ ግብር ነው፡፡ እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ፣ ዘንድሮም ኢትዮጵያውያን እ.ኤ.አ. የ2011 የዳየቨርሲቲ ቪዛ ፕሮግራም ተሳታፊ መሆን ይችላሉ፡፡

**የ2011 የዲቪ ምዝገባ መቼ ይጀመራል?**

/ለዲቪ 2011/ በኢንተርኔት ምዝገባ የሚጀመረው በኢትዮጵያ አቆጣጠር አርብ መስከረም 22፣ 2002 ሲኾን፣ ምዝገባው የሚያበቃው ሕዳር 21 ቀን 2002 ይሆናል፡፡

**ለዲቪ ሎተሪ መመዝገብ የሚቻለው እንዴት ነው?**

እንደ 2010 የዲቪ ፕሮግራም፣ መመዝገብ የሚቻለው በኢንተርኔት ብቻ ነው፡፡

አመልካቾች የኤሌክትሮኒክ ዳይቨርሲቲ ቪዛ (EDV-Form DS-5501ን) በመሙላት መመዝገብ ይችላሉ፡፡ የመመዝገቢያው ቅጽ በኢንተርኔት ላይ የሚገኘው ምዝገባው ከሚጀምርበት ከአርብ መስከረም 22፣ 2002 ጀምሮ እስከምዝገባው ወቅት ማብቂያ ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡ የመመዝገቢያ ቅጾችና መመሪያዎች ሊገኙ የሚችሉት በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ድረ-ገጽ አማካይነት ሲኾን፣ አድራሻውም የሚከተለው ነው፡- http://www.dvlottery.state.gov/ በተጨማሪም የአሜሪካ ኤምባሲ ድረ-ገጽ ውስጥ በመግባት ይህንኑ የኢንተርኔት አድራሻ ማግኘት ይቻላል፡- http://ethiopia.usembassy.gov/

**የዲቪ ማመልከቻ ተቀባይነት ማግኘት አለማግኘቱን በኢንተርኔት ማረጋገጥ ይቻላልን?**

አመልካቾች የማመልከቻ ቅጹን ሞልተው እንደላኩ በሚሰጣቸው የአመልካች ማረጋገጫ ቁጥር በመጠቀም በhttp://www.dvlottery.state.gov/ ድረ-ገጽ ውስጥ ማመልከቻቸው የሚገኝበትን ደረጃ ለመከታተል ይችላሉ።

በኢንተርኔት አማካይነት ከማረጋገጥ በተጨማሪ፣ በዳይቨርሲቲ ቪዛ የተመረጡ አመልካቾች በግንቦት እና በሐምሌ ወር 2002 መካከል ባሉት ጊዜያት ውስጥ አሸናፊነታቸውን እንዲያውቁ ይደረጋል። ለዲቪ ሎተሪ አመልክተው ዕጣው የወጣላቸው ተመዝጋቢዎች ወደ አሜሪካ ለመጓዝ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ጨምሮ የተለያዩ መመሪያዎችን እንዲያገኙ ይደረጋል። **ልብ ይበሉ። የዲቪ ዕጣ የወጣላቸው አመልካቾች በምንም ዓይነት ውጤታቸው በኢሜይል አይነገራቸውም። በሌላ በኩል ዕጣ ላልወጣላቸው አመልካቾች ምንም ዓይነት መረጃ እንዲደርሳቸው አይደረግም።** ከላይ በተጠቀሰው ድረ-ገጽ 'Diversity Visa Lottery Instructions' በሚለው አብይ ርዕስ ስር፣ 'Selection of Applicants' (‹‹የአመልካቾች መረጣ››) በሚል ንዑስ ርዕስ የዲቪ የጊዜ ሰሌዳ እና ዝርዝር ሒደትን የተመለከተ መረጃ ማግኘት ይቻላል።

**ለዳይቨርሲቲ ሎተሪ ብቁ የሚያደርጉ ነገሮች ምንድን ናቸው?**

እያንዳንዱ የዲቪ ሎተሪ አመልካች ቢያንስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቀ፣ ወይም ከዚህ ጋር ተመጣጣኝነት ያለው ትምህርት የወሰደ፣ ወይም ቢያንስ የሦስት ዓመታት ስልጠናን በሚፈልግ የሙያ መስክ የሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያለው መሆን እንዳለበት የዲቪ ሎተሪ ሕግ እና መመሪያ ተነድግጓል። ለምዝገባ የሚያበቁ ሌሎች የሥራ መስፈርቶችን የበለጠ ለማወቅ የዳይቨርሲቲ ቪዛን ድረ ገጽ http://www.dvlottery.state.gov/ ይጎብኙ።

**በዲቪ ሎተሪ መመረጥ ቪዛ ለማግኘት ዋስትና ይሆናልን?**

አይሆንም። የትምህርትና የሥራ ልምድ መመዘኛዎችን ማሟላትዎን ለአሜሪካ ቆንስላ ቢሮ ማረጋገጥ ይኖርብዎታል። በተጨማሪም የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት አዲስ አበባ በሚገኘው ኤምባሲው አማካይነት ቪዛ ከመሰጠቱ በፊት የአመልካቹን ጉዳይ መርምሮ የማጣራት መብቱ የተጠበቀ መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል። ከዚህ ቀደም፣ አመልካቾች በቃለ መጠይቅ ሒደት ወቅት የተጭበረበሩ የትምህርት ማስረጃዎችን፣ አጠራጣሪ የጋብቻ ግንኙነቶችን እንዲሁም ሌሎች የሐሰት ማስረጃዎችን አቅርበው በመገኘታቸው ቪዛ መከልከላቸው ይታወቃል።

**የዲቪ 2011 ሎተሪ ከ2010 □ዲቪ ሎተሪ በምን ይለያል?**

የዲቪ 2011 ሎተሪን ለየት የሚያደርገው በዚህኛው ምዝገባ ተመዝጋቢዎች የኢሜል አድራሻ ማካተት የሚኖርባቸው መሆኑ ነው። የአሜሪካ መንግስት ልክ እንደቀድሞው ለዲቪ ሎተሪው እድል ለሚመረጡትም ሆነ ቀጠሮ ወረቀት ለሚላክላቸው ሰዎች በፖስታ አድራሻ መልእክቱን የሚልክ ሲሆን በኢሜል አድራሻቸው ግን ጥያቄዎችንና ማብራሪያዎችን ሊያስተላልፍ ይችላል። በኢሜል የሚላኩት መልእክቶች ሁሉ ከአሜሪካ መንግስት ብቻ ሲሆኑ ምንም አይነት የገንዘብ ክፍያ አይጠየቁም።

###